# አንቺ መሞት እንጂ ማልቀስ የለብሽም እንዲሉ ሆኖብን እንጂ…

መታፈሪያ (ከጫንጮ)

አንድ ያስገረመኝን ገጠመኝ በዚሁ ፅሁፌ ልተርክላችሁ ፈቀድሁ፡፡ አንድ ወቅት ላይ አንድ ሕንዳዊ መምህራችን በአለም ላይ ዴሞክራሲ የሚባል ነገር የሌለባት አገር ታውቃላችሁን ሲሉ ጠየቁን፡፡ ለመልስ ስንዘጋጅ እሳቸው  ጊዜ ሳይሰጡን “አሜሪካ ብቻ ናት” አሉ፡፡ አቤት ያኔ የሳቅነው ሣቅ አይረሳኝም፡፡ መምህራችን ግን ጭራሽ ተናድደው ያሉትን አስታውሣለሁ፡፡ “በምንም መመዘኛ ሂዱ አሜሪካ ዴሞክራሲ የሚባል ነገር የላትም፡፡  በርግጥ መመዘኛው ስለዴሞክራሲ መለፈፍ ከሆነ ሌላ ጉዳይ ነው፡፡ ተግባር ከሆነ ግን መሠረታዊውን ነገር አታሟላም፡፡ ለምሳሌ በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ የፖለቲካ ስልጣን  ትልቅ ግምት ይሰጠዋል፤ የፖለቲካ ስልጣን በሕዝብ እጅ መሆኑና አለመሆኑ ትልቅ መስፈርት ተደርጎ መወሰድ እስካለበት ድረስ በመንግሥት ሥልጣን ውስጥ  ሕዝብ ምን ያህል ውክልና አግኝቷል የሚለው ቁልፍ ጥያቄ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በአሜሪካ የመንግሥት ሥልጣን ቁንጮ የሆነውን ፓርላማውን ከወሰድን ምን ያህል የሕዝብ ውክልና ተንፀባርቆበታል ብንል የምናገኘው ውጤት እጅግ አስደናቂ ሆኖ ነው የምናገኘው፡፡ የወጣቶች፣ የሠራተኞች፣ የብሔር ብሔረሰቦች /የጥቁር አሜሪካውያን፣ የሕንድ፣ የሂስፓኒክ አሜሪካውያን ወዘተ/ ውክልና የለም፡፡ የሴቶች ውክልናም እኛ እንድንሆን ከሚፈልጉት ሩቡን ያህል እንኳ አይሆንም፡፡ በአጠቃላይ ምክር ቤቶቻቸው በአብዛኛው አዛውንት ከበርቴዎች ወይም አሰሪዎች  ብቻ የተሰባሰቡበት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በፖለቲካ ፓርቲ ተደራጅቶ ለመንቀሳቀስ ከፍተኛ ሃብትን የሚጠይቅ በመሆኑ ውድድሩ ውስጥ ለመግባት ጨርሶ የሚታሰብ አይደለም…” ቀጠሉ መምህሩ፡፡ እኛ ግን ጭራሽ እብድ መስለው ይታዩን ነበር እንጂ ከልባቸው አልመሰለንም፡፡ ለምን እኛ የምናውቀው አሜሪካ የዴሞክራሲ ቁንጮና ጠበቃ መሆኗን ብቻ ነው፣ በወቅቱ ልባችን ሸፍቶ የነበረው ወደዚያ ለመሄድ ነበር፡፡ ምኞታችን ሁሉ ምናለ አገራችን እንደአሜሪካ በሆነች የሚል ነው፡፡ ያኔ የሳቅሁት በራሴ ላይ እነደነበር የተረዳሁት በእድሜ ብዛት በኋላ ነበረ፡፡ በያንዳንዱ ጉዳይ ጥልቅ ጥናት ያደረገ ሁሉ ግን የሚረዳው ሕንዳዊው መምህራችን የነገሩንን እውነታ

ትክክለኛነት ነው፡፡ ጥልቅ ጥናት ያላደረገ ወይም እውነቱን ጠጋ ብሎ ያላየው ግን በቀላሉ በእኔ አባባል ሊስቀብኝ እንደሚችል አምናለሁ፡፡

ሰሞኑን አንዴ ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በማስከተል ደግሞ ሂዩማን ራይትስ ዎች  ከተባለው የእነሱው ድርጅት  አገራችንን ኢትዮጵያን አስመልክቶ የሰብአዊ መብቶች ተጥሰዋል የሚል ሪፖርት ቀርቧል፡፡

የአገሬ ሰው "አንቺ መሞት እንጂ ማልቀስ የለብሽም" እንደሚለው ሆኖ አገሬ ኢትዮጵያ በአሜሪካ ላይ ጣቷን መቀሰር አትችልም እንጂ አሜሪካ ውስጥ የሚፈፀመው የሰብአዊ መብት ረገጣ ወደር የማይገኝለት መሆኑ በተጋለጠ ነበር፡፡ ግና ይህን የማድረግ ፍላጎቱ ወይም አቅሙ ያለው አገር እስካሁን ያለ አይመስለኝም፡፡

ቢሆንም ግን ምን ያህል የከፋ የሰብአዊ መብት ረጋጭ አገር እንደሆነች በበኩሌ ያደረግሁት ጥናት ውጤት እጅግ አስደንጋጭ ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ ደግሞም እንደአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አሊያም እንደሂዩማን ራይትስ ዎች መረጃዎቼን ያሰባሰብኩት የጥቅም ግንኙነት ካላቸው  ግለሰቦች /ተቃዋሚ ፖለቲከኞች/ አይደለም፡፡ ከራሳቸው መንግሥታዊ  ተቋሞቻቸው ነው፡፡ /እዚህ ላይ እነሱ ግን መንግሥታዊ መረጃዎችን ማጣራት ቀርቶ ሚዛናዊ ለማድረግ እንኳ የመንግሥትን ምላሽ ለማካተት አልሞከሩም፡፡ ለምን ቢባል ስላልፈለጉ/

የአሜሪካ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ራሱን የዓለም የሰብአዊ መብት ዳኛ አድርጎ ያቀረበው በዚህ ዓመት ብቻ አይደለም፡፡ ሁሌም በየዓመቱ የተለመደ ተግባሩ ሆኗል፡፡ ሌላው መታወቅ ያለበት ጉዳይ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተካሄዷል በሚል ሪፖርት ይፋ ያደረገው በመላው ዓለም የሰብአዊ መብት ይዞታን የመቆጣጠርና የመከታተሉን ኃላፊነት ለየመስሪያ ቤቶቹ ሸንሽኖ ያከፋፈለው የአሜሪካን መንግሥት /የሲአይኤ አመታዊ ሪፖርት፣ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሪፖርት፣ የሰብአዊ መብት ጥበቃን አስመልክቶ ቋሚ መግለጫ የሚያወጣበት አካል አላየሁም፡፡

በአሜሪካ ስላለው ተጨባጭ የሰብዓዊ መብት አያያዝ ሰፋ ያለ ጥናት ማካሄድ አቅምን የሚጠይቅ ቢሆንም በበኩሌ ማሳያ የሚሆኑ ጉዳዮችን ብቻ ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡

<u>በህይወት የመኖር፣ ሃብት የማፍራትና የግለሰብ ሕይወት ጥበቃ መብት</u>

አሜሪካ ውስጥ የዜጐች በሰላም የመኖር መብት ፣ ሃብታቸው የመጠበቅና የግለሰብ ሕይወት ጥበቃ የሚባሉት ነገሮች ቀላል አይደሉም፡፡ ከሌላ ምንጭ ሳይሆን በራሱ በአገሪቱ የፍትህ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ሴፕቴምበር 2009 ታትሞ የወጣው ሪፖርት እንዳመለከተው እ.ኤ.አ በ2008 ዓመት ውስጥ ብቻ አሜሪካ ውስጥ በነዋሪዎች ላይ የተፈፀመው ኃይል የተቀላቀለበት የወንጀል ድርጊት ብዛት 4 ነጥብ 9 ሚሊዮን፣ በንብረት ላይ የተፈፀመ ወንጀል ብዛት 16 ነጥብ 3 ሚሊዮን፣ በግለሰቦች ላይ የተፈፀመ የስርቆት ወንጀል ብዛት ደግሞ 137 ሺህ ነው፡፡ ኃይል የተቀላቀለበትን ወንጀል ነጥለን ብንመለከት እድሜያቸው 12 ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆኑ 1000 ሰዎች መካከል 19 ነጥብ 3 በሚሆኑት ላይ ተፈጽሟል፡፡ ይህንን ከሚኒስቴሩ ዌብሳይት /http፡ //www.ojp.usdoj.gov/ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል በዚያው ዓመት ከተፈፀሙት ወንጀሎች/ የትራፊክ ወንጀልን ሳይጨምር/ በተያያዘ በፖሊስ የተያዙት ሰዎች ብዛት ከ14 ሚሊዮን በላይ እንደሆነ የአሜሪካ የፌዴራል የወንጀል ምርመራ ቢሮ /ኤፍቢአይ/ን ዌብሳይት /http://www.fbi.gov/ መመልከት ይቻላል፡፡

<u>2. የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች</u>

አሜሪካ ውስጥ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ምን ያህል እንደሚጣሱ ቀጥሎ የቀረቡትን መረጃዎች እንመልከት፡፡

ለአብነት ያህል በኒውዮርክ ከተማ በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ ከመጠን በላይ ኃይል ተጠቅመዋል በሚል አቤቱታ የቀረበባቸው ፖሊሶች ብዛት 315 ነው፡፡ የኒውዩርክ ፖሊስ መምሪያ ኖቬምበር 17 ቀን 2009 ባወጣው የፖሊሶች የጦር መሣሪያ

አጠቃቀም ሪፖርት ላይ እንደገለፀው በከተማይቱ ውስጥ እ.ኤ.አ በ2007 ብቻ ፖሊሶች 588 ጥይቶችን ተኩሰው፣ 10 ሰዎችን ሲገድሉ በ2008 ዓ.ም አሃዙ ቀነስ በተባለበት ዓመት የተኰሱት ጥይት ብዛት 354፣ የገደሉት ሰው ብዛት ደግሞ 13 ነው፡፡ ይህ እንግዲህ በጥይት የሞቱትን ብቻ እንጂ የቆሰሉትን አይጨምርም፡፡ በተጨማሪም በቆመጥና በሌላ ነገር የተገደሉትን ወይም የቆሰሉትን አያካትትም፡፡ በዚያ ላይ በየጊዜው በፖሊስ የተፈፀሙ ፍፁም አረመኔያዊ ድርጊቶች አሉ፡፡ ለአብነት ያህልም የሳንሆዜ ከተማ አራት ፖሊሶች ስፕቴምበር 3 ቀን 2009 ዓ.ም በአንድ የሳንሆዜ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ላይ የፈፀሙት ድብደባ ተጠቃሽ ሲሆን ፖሊሶቹ በቆመጦቻቸውና በጠመንጃ ስደፍ ከ10 ጊዜ በላይ ተቀጥቅጧል፡፡ አምነሲቲ ኢንተርናሽናል እንዳለው ከሆነ እ.ኤ.አ በ2009 የመጀመሪያዎቹ 10 ወራት ውስጥ ብቻ በአሜሪካ ውስጥ በፖሊሶች በቴዘር ጠመንጃ የተገደሉት ሰዎች ብዛት 45 ደርሷል፡፡ ከነዚህ መካከልም አንዱ የ15 ዓመት ታዳጊ ነበር፡፡

የሕግ አስከባሪዎች የሥልጣን መባለግም እንደጉድ የበዛባት አገር ናት- አሜሪካ፡፡ ጉቦኝነትና አስፈራርቶ ገንዘብ መቀበል በአሜሪካ የሌለ የሚመስለን ብዙዎች ነን፡፡ የእነሱን ያህል ግን በሌላ ቦታ መኖሩን እግዜር ይወቅ፡፡

የእስረኞች አያያዝ በኢትዮጵያ ጥሩ አይደለም ብሎ የሚወነጅለን የአሜሪካ መንግሥት የራሱን ጉድ እናውራ ካልን ፍፁም ትዝብት ላይ የሚጥለው ነው፡፡ ዲሴምበር 8 ቀን 2009 የአገሪቱ የፍትህ ሚኒስቴር ያወጣው መረጃ በ2008 ዓ.ም መጨረሻ በመላ አገሪቱ የነበረው የእስረኞች ብዛት 7 ነጥብ 3 ሚሊዮን ነበር፡፡ ከነዚህ ውስጥ ወህኒ ውስጥ ብቻ የሚገኙት 2 ነጥብ 3 ሚሊዮን ናቸው፡፡ ይህ ማለት ከ198 አሜሪካውያን መካከል አንዱ የሚኖረው ወህኒ ውስጥ ነው፡፡ አጃኢብ አሉ! የእኛ እስር ቤቶች የምግብና የመኝታ ችግር አለባቸው በሚል በድህነታችን ሊወቅሱን ፈለጉ እንጂ የገንዘብ ችግር በሌለባቸው የአሜሪካ እስር ቤቶች ያለው ሁኔታ የሚያሳየን ሆን ብሎ የሰብአዊ መብት ረገጣ እንደሚፈፀምባቸው ነው፡፡ ለአብነት ያህል የአሜሪካ የፍትህ ሚኒስቴር ባወጣው ሪፖርት እንደገለፀው የእስር ቤት ኃላፊዎች ሳይቀሩ በእስረኞቻቸው ላይ ግብረሰዶማዊ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ይፈጽማሉ። በነገራችን ላይ አሜሪካ ውሰጥ 93 የፌዴራል ወህኒ ቤቶች

አሉ፡፡ በእስር ቤቶች የሚፈፀመው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ባለፉት ስምንት ዓመታት ውስጥ በእጥፍ ጨምሯል፡፡ በማስረጃ ተረጋግጦባቸው በአንድ ዓመት ውስጥ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት የታየ የወህኒ ኃላፊዎች ቁጥር 90 በግብረሰዶማዊ 40ው የአስገድዶ መድፈር ጥቃት በተጨማሪ ሌሎች ወንጀሎችንም የፈፀሙ ናቸው፡፡

በእስር ቤት ያለው ሁኔታ ለኤች አይቪ ኤድስ መስፋፋት መንስዔ እንደሆነም የአሜሪካ የፍትህ ሚኒስቴርን ሪፖርት መመልከቱ በቂ ነው፡፡ በሪፖርቱ መሠረት እ.ኤ.አ በ2008 መጨረሻ ላይ በአሜሪካ የፌዴራልና የክልል እሥር ቤቶች ውስጥ 20 ሺህ 231 ወንዶችና 1ሺህ 913 ሴት ታራሚዎች የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ተገኝቶባቸዋል፡፡ የሚያስገርመው የሂዩማን ራይትስ ዎች ማርች 24 ቀን 2009 ዓ.ም ባወጣው ሪፖርት እንዳመለከተው እነዚህም ሆኑ ሌሎች ታራሚዎች በቂ ሕክምና አያገኙም፡፡

የማይገሰሰው የዜጐች የመልዕክት ልውውጥ ግላዊነት የኢንተርኔት ነፃነት ደቀመዝሙር ነኝ የምትለው አሜሪካ ዜጐቿን የመልዕክት ልውውጥ በመጥለፍ መንግሥት የገዛ ዜጐቹን በግላጭ የሚሰልልበት አገር አሜሪካ ብቻ ናት፡፡ የአሜሪካ የብሔራዊ ደህንነት ድርጅት /NSA/ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የግለሰቦችን ምስጢሮች የሚያነፈንፉ መሣሪያዎችን ተክሏል፡፡ በዚህም እያንዳንዱ የግለሰብ የስልክ ንግግር ፣ የፋክስ መልዕክት፣ ኢ-ሜይል ወዘተ ይበረበራል፡፡ ይህን የምናውቅ ስንቶቻችን ነን? ብርበራው የተጀመረው እ.ኤ.አ በ2001 ሽብርተኝነትን ለመከላከል በሚል በጥቂት አረብ አሜሪካውያን ላይ የተጀመረው ይህ የመልዕክት ግንኙነት ጠለፋ ዛሬ እያንዳንዱን አሜሪካዊ ዜጋ የሚመለከት ሆኗል፡፡ በዚህ ሥራ ላይ የአሜሪካ የጦር ኃይል ሳይቀር ይሳተፋል፡፡

የፕሬስ ነፃነት ምን ያህል እንደሚታፈንና አሜሪካ ሌሎች አገሮችን ለማጥቃት ብቻ እንደምታላዝንበት ተጨባጭ ማስረጃ ላቅርብ፡፡

አሜሪካ በኢራቅና አፍጋኒስታን የምታካሂደው ጦርነት ተቃውሞ እንዳይገጥመው በማሰብ በእነዚህ አገሮች የሚካሄደውን የሚዲያ መረጃ የሚያቀርቡት "ኢምቤድድ ጆርናሊስትስ" የተባሉ የቀድሞ ወታደሮች ስፔንታጐን ተመልምለው የቲቪና የሬዲዮ ከሜንታተሮች ሆነው እንዲሰሩ ማድረግ ነው፡፡ ዓላማውም "አዎንታዊ ትችቶችን" በማቅረብ ዕውነታውን ከዜጐች እይታ ለመሸፈን መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በዚህም የአሜሪካ ሕዝብ ጦርነቶቹን እንዲደግፍ ለማድረግ ነው /ኒውዮርክ ታይምስ ኤፕሪል 20 ቀን 2009 ይመልከቱ/

ከዚህ በላይ ደግሞ የአሜሪካን ብሔራዊ ጥቅም ይፃረራሉ የተባሉ የአረብ ሳተላይት የቴሌቪዥን ቻነሎች ለአሜሪካ ሕዝብ እንዳይሰራጩ የአሜሪካ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ2009 አንድ ረቂቅ ሕግ አውጥቷል፡፡ ይህ በ4 ድምፀ ተቃውሞ በኮንግረሱ ሙሉ ድጋፍ ያለፈውና በሴኔቱ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት /ይፀድቃል ተብሎ የሚጠበቀው ሕግ ፀረ - አሜሪካዊ ስሜትን ያራግባሉ ወይም በአሜሪካ አጋር አገሮች ላይ ጥላቻና ይነዛሉ የተባሉ የአረብ ጣቢያዎችን ጃም የማድረግ ስልጣንን ለመንግሥት ያጎናፅፈዋል፡፡ ይህን አይነቱን እርምጃ "ህጋዊ" ካባ እስኪሰፋለት የመጠበቅ ትዕግስት ያልነበረው የአሜሪካን አስተዳደር በሊባኖስ ውስጥ በህጋዊ መንገድ ተመዝግቦ የፓርላማ መቀመጫ የያዘው የሂዝቡላ ፓርቲ ንብረት ነው የሚባለውን የቲቪ ስርጭት እንዲታገድ ያደረገ ሲሆን የሃማስ ቴሌቪዥንም ወደ አሜሪካ እንዳይሰራጭ የደፈቃ እርምጃ ወስዷል፡፡ የዚህ የአሜሪካ መንግስት እርምጃ ሰለባ ከሆኑት ጣቢያዎች መካከልም አልጀዚራም ተጠቃሽ ነው፡፡ እንግዲህ በአሜሪካ ለብሔራዊ ደህንነት ተወሰደ የተባለው እርምጃ በሌላ አገር ሲወሰድ ግን እንደ ሰብአዊ መብት ረገጣ ተብሎ በስቴት ዲፓርትመንት ሪፖርት የሚቀርበው በዚህ መልኩ ነው፡፡

<u>የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ እና ባህላዊ መብቶች</u>

የአሜሪካ የሠራተኛ ጉዳይ ቢሮ ኖቨምበር 6 ቀን 2009 ባወጣው ሪፖርት 16 ሚሊዮን ሕዝብ ሥራ አጥ ነው፡፡ በድህነት ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ 39.8 ሚሊዮን ነበር በ2008 / ዋሽንግተን ፖስት ሴፕቴምበር 10 ቀን 2009ን ይመልከቱ/፡፡

የድህነቱ መጠን እጅግ የከፋ ከመሆኑ የተነሳ ራሱን የሚገድለው አሜሪካዊ ብዛት እየጨመረ ሄዶ በየአመቱ ራሱን የሚገድለው ሕዝብ ብዛት 32 ሺ.ህ ገደማ ደርሷል / ታይም መጽሔት http://www.time.com/

በአሜሪካ የግብርና ሚኒስቴር ኖቬምበር 6 ቀን 2009 ሪፖርት መሠረት በ17 ሚሊዮን ቤተሰቦች ውስጥ /ወይም ከጠቅላላው ቤተሰብ 14 ነጥብ 6 የሚሆነው/ የሚኖር 49 ነጥብ 1 ሚሊዮን ሕዝብ የበቂ ምግብ አቅርቦት ችግር ያለበት ነው፡፡ 36 ነጥብ 5 ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝብ በኩፖን ምግብ የሚቀበል ተረጂ ነው፡፡

የዘረኝነት ጉዳይም እንዲሁ አይጣል የሚያስብል ነው- በተለይም በቁጥር አሜሪካውያንና በሌሎች አናሳ ብሄሮች ላይ የሚፈፀመው የትየሌለ ነው፡፡ በቤት አሰጣጥ፣ በህክምና፣ በሥራ ቅጥር፣ በትምህርት፣ ወዘተ... አድልኦ ይፈፀምባቸዋል፡፡ ክስ ሳይቀርብባቸው ለብዙ ጊዜ በእስር የሚቆዩ አሉ ዜጎች ብዙ ናቸው፡፡ /ኒውዮርክ ታይምስ ኖቬምበር 2 ቀን 2009/ ስደተኞች እየታነቁ በግዞት ወደአገራቸው ከመላካቸውም በላይ እስር ቤት ውስጥ የሚሞቱ አሉ፡፡ ለምሣሌ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ 104 ስደተኞች በእስር ቤት ሞተዋል / ወልስትሪት ጆርናል ኦገስት 18 ቀን 2009/

<u>የሴቶችና የህፃናት መብት</u>

ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል የማኅበራዊና የፖለቲካዊ መብት ተጠቃሚዎች አይደሉም፡፡ ሴቶች ከጠቅላላው የአሜሪካ ሕዝብ ውስጥ 51 በመቶ ያህሉን ቢይዙም፤ አሁን በሥራ ላይ ባለው 111ኛው የአሜሪካ የሕግ ምክር ቤት መቀመጫ ያላቸው 92 ብቻ ወይም 17 በመቶ ያህሉን መቀመጫ የያዙ ናቸው፡፡

በሥራ ቅጥር ሴቶች ላይ አድልኦ እንደሚፈፀምባቸውም የአሜሪካ የሥራ ዕድል እኩልነት ኮሚሽን ያወጣውን መረጃ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይኸው መንግሥታዊ

ድርጅት ኖቬምበር 3 ቀን 2009 ባወጣው ሪፖርት እንዳመለከተው አድልኦ ተፈፅሞብናል በሚል አቤቱታ ያቀረቡት ግለሰቦች ብዛት እ.ኤ.አ በ2008 አም 95 ሺህ 402 ነው፡፡

በሴቶች ላይ የኃይል ጥቃትና የወሲብ ጥቃት ከሚፈፀምባቸው አገራት አሜሪካ ከፍተኛውን አሃዝ የያዘች አገር ስትሆን በእንግሊዝ ከሚፈፀመው በ13 እጥፍ፣ በጃፓን ከሚፈፀመው ደግሞ በ20 እጥፍ ብልጫ አላት፡፡

በህፃናትም ዘንድ የሚፈፀመው የመብት ረገጣ እንደዚሁ አስገራሚ ነው፡፡ ለምሣሌ ያህል የአሜሪካ የግብርና ሚኒስቴር ባወጣው ሪፖርት በአሜሪካ ውስጥ 16 ነጥብ 7 ሚሊዮን ህፃናት እ.ኤ.አ በ2008 በቂ ምግብ አልነበራቸውም፡፡ ይኸውም በአሜሪካ ካለው ጠቅላላ ሕፃናት ውስጥ ሩብ ያህሉን የያዘ ነው፡፡ በዚያ ላይ የኃይል ጥቃት ይፈፀምባቸዋል፡፡ በ2008 ዓ.ም የተገደሉ ሕፃናት ቁጥር 1ሺ494 ሲሆን እነዚህ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑት ናቸው፡፡ /ዩኤስቱዴይ አክቶበር 8 ቀን 2009/

የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛውም አያድርስ ነው፡፡ በግለሰቦች እርሻዎች ላይ ተቀጥረው የሚሰሩ ጨቅላ ሕፃናት ቁጥር 400ሺህ ይደርሳል፡፡ ከነዚህ ውስጥ የስምንት ዓመት ጨቅላዎች ይገኙበታል፡፡

<u>የሌሎች ዜጐች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት</u>

አሜሪካ ባላት ከፍተኛ ወታደራዊ የበላይነት በመተማመን የበርካታ አገራትን ሉዓላዊነት በመጣስና የእነዚህኑ አገራት ዜጐች ሰብዓዊ መብቶች በመርገጥ ወደር ያልተገኘላት አገር ናት፡፡

በዚያ ላይ የዓለማችን ቁጥር አንድ መሣሪያ ነጋዴ በመሆን የብዙ አገራትን ዜጐች የምታጫርስ እስዋ ናት፡፡ የሌሎች አገራትን ዜጐችን በእስር ቤት በማጎር የምትፈጽመው የሰብዓዊ መብት ረገጣ ዘግናኝ ነው፡፡ በጓንታናሞ በሚገኙ እና

በሌሎች በርካታ እስር ቤቶች በእስረኞች ላይ የፈፀመችው የመብት ረገጣ በሌላ አገር ቢፈፀም ምን ሊባል ይችል እንደነበር ለመገመት አይከብድም፡፡ እስረኞችን ራቁታቸውን ሙሉ ቀን፣ሙሉ ሌሊት ጐብጠው እንዲቆዩ፣ እስከ11 ቀናት እንቅልፍ እንዲያጡ በመከለከል፣ ሳንባዎቻቸው በውሃ በመሙላት የተደረጉ ቅጣቶች በምድራችን ላይ የተፈፀሙ ዘግናኝ ቅጣቶች ተምሳሌት ናት አሜሪካ፡፡ እስረኞችን አፍኖ ለማናዘዝ በሚደረግ ሙከራም ብዙዎች ህይወታቸውን አጥተውባታል አሜሪካ፡፡ በሲአይኤ የሚሰጠው ሽፋን ራሳቸውን ገደሉ እየተባለ ነው፡፡ ጉዳዩ ለህዝብ ይፋ እንዳይወጣ ሲባል በሲአይኤ 92 የቪዲዮ ካሴቶች እንዲቃጠሉ መደረጋቸውንም አንረሳውም፡፡

አንዱ እስረኛ "የምድራችን ገሃነም" ሲል በገለፃቸው እሥር ቤቶች የብዙዎች ሕይወት ያለፍርድ ጠፍቷል፣ አካላቸው ጎድሏል ወዘተ…

በአጠቃላይ አሜሪካ በሰብአዊ መብት አያያዝ ረገድ የራሷ እያረረባት የሰው ታማስላለች እንዲሉ መንግሥቷ ስለራሱ ምንም ሳይል ሌሎችን ለመኮነን ይሞክራል፡፡ ይህንን ለማድረግ ግን አንዳችም ሞራላዊ ብቃት የለውም፡፡ ከዚህ በመነሳት ነው እንግዲህ የአሜሪካ የሰብአዊ መብቶች ሪፖርት በአገራችን ጉዳይ ጣልቃ ከመግባት ውጭ ፋይዳ የላቸውም የምለው፡፡ ሪፖርቱ የሚያጋልጠው የአሜሪካን ግብዝነት ብቻ ነው የምለውም ለዚህ ነው፡፡